የአውሮፓ ሕብረት
የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በኢትዮጵያ 2002 ዓ.ም.
የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ

**ለአስቸኳይ መግለጫ**

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የዘንድሮው የኢትዮጵያ ምርጫ በጣም የተደራጀ ግን ደግሞ የመወዳደሪያ ሜዳ ያነሰበት ተብሎ ይገለፃል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓ.ም.** - የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የምርጫው ቀን ሰላማዊ ፣ የተረጋጋና በጣም በርካታ ህዝብ የህዝብና የክልል ም/ቤት ተወካዮቹን ለአራተኛ ጊዘ ሲመርጥ የዋለበት ነው፡፡

“የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲ ያሳየውን ቁርጠኝነት አደንቃለሁ - በጣም በርካታ ህዝብ ወጥቶ መመዝገቡና በሰላም መጥቶ ለዲሞክራሲያዊ መብቶቹ መረጋገጥ ያሳየው ተነሳሽነት የሚደነቅ ነው “ ብለዋል ዋና ታዛቢ ታይስ በርማን፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ምርጫውን ያካሄደው ብቁና ሙያዊ በሆነ መልኩ ቢሆንም የተወሰኑ ቴክኒካዊ አጥረቶች ነበሩበት፡፡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ በየክልሉ ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ከክልል ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አመኔታ አላገኙም፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በደረሰበት ውጤት መሰረት ምርጫው የተወሰኑ ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን ያሟላ አይደለም - በተለይም ሂደቱ ግልጽነት የጎደለውና የመወዳደርያ ሜዳ ያነሰበት በመሆኑ፡፡

ምርጫው ከመካሄዱ በፊት የነበረው የፖለቲካ ድባብ በአጠቃላይ የተረጋጋና ሰላማዊ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የደህንነት ስጋቶችና ማስፈራሪያዎች እያደገ ከመጣ የቅሬታዎች ቁጥር ጋር አስተናግዶዋል፡፡

በአጠቃላይ የምርጫ ቅስቀሳው ሰላማዊ የነበረ ቢሆንም በተወሰነ መልኩ ያልተጋጋለ የምርጫ ዘመቻ ነበር፡፡ የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ እንዳስተዋለው ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ የመንግስትን ሀብት ለምርጫ ዘመቻ ይጠቀም ነበር፡፡ ይህም የመወዳደርያው ሜዳ እንዳይስተካከልና ለኢሕአዴግ አንዲያደላ አድርጎታል፡፡

በአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ትዝብት መሰረት ሚዲያው የምርጫ ቅስቀሳውን ሲዘግብ የገለልተኛነትን ድምፀት ያሳየ ቢሆንም የመንግስት ሚዲያው ከ50 ከመቶ በላይ ሽፋን የሰጠው ለገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ነበር፡፡ ሚዲያዎች ዘገባዎቻቸው ጥንቃቄ የተሞላባቸው ነበሩ፡፡ የኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ ለ63ቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች በጣም በርካታ የአየር ሰዓት የሰጣቸው ቢሆንም የፕሪንትም ሆነ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው በመላ አገሪቱ የማይዳረስ መሆኑ መራጮች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ምርጫ እንዳያደርጉ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የምርጫው አጠቃላይ ውጤት አስኪነገር ድረስ አገር ውስጥ ይቆያል፡፡ አጠቃላይ የምርጫው ሂደት በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ለመገናኛ ብዙሀን ጥያቄዎች ወ/ሮ አግነስ ዶካን ያነጋግሩ
ስልክ፡- +251 (0) 920 537 623
E-mail : agnes.doka@eueom-ethiopia.org